# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁ. 141625

ሐምሌ 26 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ
መስጠፋ አህመድ
አብርሃ መሰለ
ፊይሳ ወርቁ
ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ አድና መላኩ
ተጠሪ፡- የወልዲያ ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት----ከክልሉ ፍትህ ቢሮ ፍሬህይወት አበባቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የወልዲያ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0104064 በቀን 24/02/2009 ዓ.ም ጉዳዩ በቀጥታ ክስ በፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም በማለት የሰጠውን ብይን ፣የሰሜን ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 19155 በቀን 27/04/2009 ዓ.ም በፍርድ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 03-16739 በ27/06/2009 ዓ/ም በትእዛዝ በማጽናታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የዳኝነት ሥልጣንን የሚመለከት ሲሆን በስር ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የክሱ ይዘትም፡- በወልዲያ ከተማ 06 ቀበሌ ክልል ውስጥ የሚገኘውና አዋሳኙ በክሳቸው የተጠቀሰው ቦታ እንዳላቸውና በዚህ ቦታ ላይ ቤት ያላቸው፣ ባህር ዛፍና ሁለት እግር ጽድ ያፈሩ መሆኑን ይዞታውን ለረዥም ጊዜ ይዘው በሚገኙበት ሁኔታ ተጠሪ ህግና መመሪያን መሰረት ሳያደርግ፣ ለአመልካችም 500 ካ/ሜትር ይዞታ ሳይጠብቅላቸው ቦታውን እየሸነሸነ ለግለሰቦች እየሰጠ እንደሚገኝ፣ በቦታው ላይ የሰሩትን ቤት ያለምንም ምክንያት በዶዘር መጋቢት ወር 2007 ዓ/ም ያፈረሰባቸውና አቤቱታቸውን ለሚመለከተው አካል አቅርበው የሚመለከታቸው አካላት እንደማንኛውም ባለይዞታ 500 ካ/ሜትር ይዞታ ለአመልካች እንዲጠበቅላቸው አስተዳደራዊ ውሳኔ የሰጡ መሆኑንና በዚህ አግባብ እንዲወሰንላቸው ለተጠሪም ሆነ ለሚመለከተው አካል አመልክተው መፍትሔ ያላገኙ መሆኑን ገልጸው ለክሱ ምክንያት ከሆነው ነባር ይዞታ ላይ 500 ካ/ሜት እንዲጠበቅላቸው፣ ከሕግ ውጪ በዶዘር ለፈረሰባቸው ቤት ግምት ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር)፣ የባህር ዛፉና የፅዱ ግምትም እንዲከፈላቸው እንዲሁም ከ500 ካ/ሜትር በላይ ላለው ይዞታም ካሳ እንዲከፈላው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 እና በአዋጅ ቁጥር 455/97 መሰረት በፍርድ ቤት በቀጥታ ክስ የሚታይ ያለመሆኑን፣ አመልካች በቦታው ላይ መብት የሌላቸው መሆኑንና ሌሎች የክርክር ነጥቦችን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ስልጣንን መሰረት አድርጎ የተነሳውን የተጠሪን መቃወሚያ መርምሮ አመልካች

*የከተማ ቦታ ይዞታን እንዲለቁ የተደረጉ በመሆኑ ጉዳዩ መታየት ያለበት በከተማ አስተዳደሩ ስር ለተቋቋመ የመሬት ነክ አቤቱታ ሰሚ አካል ነው እንጂ ለፍርድ ቤት አይደለም የሚል ምክንያት አስፍሮ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በቀጥታ ክስ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም ሲል በብይን የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን ተገቢ ነው በማለት አጽንቶታል፡፡ በመጨረሻም አመልካች የሠበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው በአጣሪው ችሎት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የአመልካች ክስ መሰረታዊ ይዘት ከሕግ ውጪ የተወሰደው ቦታና የወደመው ንብረት በሕጉ አግባብ ታይቶ ባለይዞታነታቸው መብት እንዲጠበቅላቸውና ለወደመው ንብረት ደግሞ ካሳ እንዲከፈል የሚያሳይ ሁኖ እያለ የክሱን መሰረታዊ ይዘት ሳይገነዘቡ ጉዳዩ በቀጥታ ክስ በፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም በማለት መወሰናቸው ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታቸው ተመርምሮም ኣመልካች በሕገ ወጥ መንገድ ቦታዬ ተወስዶአል፣ ንብረቴም ወድሟል በማለት ያቀረቡት ክስ በአስተዳደራዊ መልኩ ብቻ የሚታይ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 721/2004 እና የሊዝ ደንብ ቁጥር 103/2004 በመጥቀስ የመወሰናቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡*

*የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባላመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ አና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡*

*ከክርክር ሂደት መገንዘብ የሚቻለው አመልካች ከነባር ይዞታቸው ውስጥ በሕጉ አግባብ ሊጠበቅላቸው የሚገባው ይዞታ መብት ያልተጠበቀላቸው መሆኑንና በይዞታው ላይ የነበሩ ንብረቶችም ኪሳራ ሳይከፈላቸው በዶዘር የወደሙባቸው መሆኑን ጠቅሰው ክስ የመሰረቱ መሆኑን፣ ተጠሪ የሚከራከረው ደግሞ ጉዳዩ ከህግ ውጪ የተያዘውን የከተማ ቦታ የማስለቀቅ ጉዳይ በመሆኑ ለተጠሪ በሕጉ ከተሰጠው ስልጣን አንፃር ጉዳዩ የከተማ ቦታን ማስለቀቅ ጉዳዮች አቤቱታ ሰሚ አካል ከሚቀርብ በስተቀር በቀጥታ ክስ በፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡*

*ፍርድ ቤቶች በህግ የሚቋቋሙ በመሆናቸው የዳኝነት ስልጣናቸው የሚመነጨውም ከህግ ነው፡፡ የማንኛውም ፍርድ ቤት ስልጣን በህግ ተወስኖ የሚሰጥ በመሆኑ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ተቀብሎ ከማስተናገዱ በፊት ጉዳዩን /ክሱን/ ለማየት በህግ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ በህግ የዳኝነት ስልጣን ሳይኖረ የሚሰጥ ውሳኔ የህግ መሰረት ያለው ነው ለማለት አይቻልም፡፡*

*ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በስር ፍርድ ቤት የጠየቁት ዳኝነት ከነባር ይዞታቸው ውስጥ 500 ካ/ሜትር እንዲጠበቅላቸውና በይዞታው ላይ የነበረው ንብረትም ከሕግ ውጪ በመወደሙ ካሳ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ነው፡፡ ተጠሪም ይዞታውን*

*ከሕግ ውጪ በመያዙ መውሰዱንና አመልካች በሕግ አግባብ የያዙት ይዞታ ደግሞ የተጠበቀላቸው መሆኑን ገልጸ ጉዳዩ የከተማ ቦታን ከማስተዳደር ስልጣኑ ጋር የተያያዘና በከተማ ቦታ ማስለቀቅ ጉዳዮች አቤቱታ ሰሚ አካል ቀርቦ ሊታይ ይገባል በማለት የሚከራከር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡*

*በመሰረቱ ካሳን አስመልክቶ የሚቀርቡ አቤቱታዎችና ይግባኝ በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 11 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በከተማ አስተዳደር የከተማ መሬት ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ካለ ካሳውን አስመልክቶ የሚቀርበው ቅሬታ ለዚህ አስተዳደራዊ አካል የሚቀርብ ስለመሆኑ ሕጉ የሚደነግግ ሲሆን የከተማው አስተዳደራዊ አካል ካሳውን አስመልክቶ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ለመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ማቅረብ እንደሚችልም ሕጉ ደንግጎ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑም ሕጉ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም በአዋጁ መሰረት ይዞታው የተወሰደው ያለአግባብ ነው በሚል መሬት እንዲለቀቅ በተላለፈው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ማቅረብ የሚቻልበት ሁኔታ በአዋጁ ውስጥ አልተካተተም፡፡*

*የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 በአንቀፅ 26() ስር አግባብ ያለው አካል ከቦታው ለሚነሳው ንብረት ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ እንዲከፈል በማድረግ የከተማ ቦታ ይዞታን ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የማስለቀቅና የመረከብ ስልጣን እንደሚኖረው ሲደነግግ በተጠቃሹ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር አራት ስር ደግሞ አግባብ ያለው አካል በሕገ ወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታ በአዋጁ አንቀጽ 27 መሰረት የማስለቀቂያ ትዕዛዝ በመስጠትና ካሳ መክፈል ሳያስፈልግ የሰባት ቀናት የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ብቻ ለባለይዞታው በአካል በመስጠት ወይም በቦታው በሰፈረው ንብረት ላይ በመለጠፍ የማስለቀቅ ስልጣን እንደሚኖረው ተመልክቶአል፡፡ የማስለቀቂያ ትዕዛዝን ወይም ማስጠንቀቂያ የሚመለከቱ አቤቱታዎች አቀራረብን በተመለከተም አዋጁ በአንቀጽ 28 ስር ያሰፈረ ሲሆን በአቤቱታዎች ላይ ስለሚኖረው ይግባኝም በአዋጁ አንቀፅ 29 ስር ሰፍሮ ይገኛል፡፡ በመሆኑም አዋጅ ቁጥር 721/2004 በሕገ ወጥ መንገድ የተያዙ የከተማ ቦታዎችን እንዲለቀቁ የሚደረግበት ስርዓት በግልጽ የተመለከተ ሲሆን አግባብ ያለው አካል በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታውን ለይግባኝ ሰሚው ጉባኤው ማቅረብ እንደሚችል ሕጉ መደንገጉ ጉዳዩ በቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት የሚሄድበት አግባብ የሌለ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው አካል ጉዳዩን የሚያስተናግደውም አቤቱታው በቅድሚያ መሬቱን እንዲለቅ ትዕዛዝ ለሰጠው አካል ቀርቦ መስተናገዱ ሲረጋገጥ መሆኑን በአዋጁ የከተማ ቦታን ማስለቀቅ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮችን በተመለከተ የተዘረጋው ስርዓት ያስገነዝበናል፡፡*

*ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ክሱን የመሰረቱት የነባር ይዞታ ባለመብትነት እንዲጠበቅላቸውና በተጠሪ የወደመ ንብረት ካሳ እንዲከፈላቸው ሲሆን የክሳቸው መሰረታዊ ይዘት የሚያስገነዝበውም የነባር ይዞታ መብትን የሚመለከቱ ህጎች የጠበቁላቸው መብቶች ሳይከበሩላቸው ሕጉቹ ተጥሰው ይዞታው የተወሰደባቸው መሆኑንና ይዞታው ሲወሰድም በላዩ ላይ የሰፈረው ንብረት የወደመባቸው መሆኑን በመሆኑ ነባር ይዞታን የሚመለከቱ ሕጎችንና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2035 ድንጋጌን መሰረት በማድረግ ጥያቄአቸውን መመርመርን የግድ የሚል ነው፡፡ ተጠሪ የከተማ ይዞታን*

የማስተዳደር ስልጣን በሕጉ አግባብ የተሰጠው ቢሆንም ስልጣንን እና ኃላፊነቱን በሕጉ አግባብ አልተወጣም የሚል ክርክር ያለው ወገን ግን ጉዳዩን በፍርድ ቤት ወስዶ መብቱን ከማስከበር የሚከለከል ያለመሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37፣ 40(3)(4)፣79(1) እና 78(4) ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች ክሳቸውን ለመደበኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርቡ የቻሉትም የሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላት የነባር ይዞታ ባለመብትነታቸው እንዲጠበቅላቸው አስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጥተው እያለ ተጠሪ ውሳኔውን ባለማክበሩ ምክንያት መሆኑን ከክሳቸው መግለፃቸው ሲታይ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀፅ 26፣ 27 እና 28 ድንጋጌዎች በተመለከተው አካል በሚመለከተው አካል በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ አላቸው ለማለት የማያስችል በመሆኑ በተጠቃሹ አዋጅ በተዘረጋው የይግባኝ ጉባኤ መብታቸውን ማስከበር አለባቸው ሊባሉ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ይልቁንም እሚመለከተው አካል ወስኖባቸው እያለ በተጠሪ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ሕጎቹ ተጥሰው የይዞታና የንብረት መብታቸው እንደተነካባቸው አመልካች በክሳቸው መጥቀሳቸውና ተጠሪም በሕጉ አግባብ ስልጣኑን በመጠቀም የወሰደው እርምጃ መሆኑን ጠቅሶ መከራከሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 246፣ 247 እና 248 ድንጋጌዎች አግባብ የተጠሪ እርምጃ ሕጉን ተከትሎ የተከናወነ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን ማጣራትን የግድ የሚል በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 ወይም አዋጅ ቁጥር 455/97 ድንጋጌዎች አግባብ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት በቀጥታ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችል አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ስለሆነም ከአመልካች ክስ መሰረታዊ ይዘት ስንነሳ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይንም ሆነ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ብይን በማጽናት የተሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚሁ መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በወልዲያ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0104064 በቀን 24/02/2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በሰሜን ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 19155 በቀን 27/04/2009 ዓ.ም በፍርድ፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 03-16739 በ27/06/2009 ዓ/ም የጸናው ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የወልዲያ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ_0104064 ክርክሩን እንዲቀጥል በማድረግ ከስልጣን ውጪ የቀረቡትን የግራ ቀኙን ሌሎች የክርክር ነጥቦችን በመመርመርና በማጣራት ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1 መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. በዚኑ ችሎት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ.መ.ቁ. 22775

ሐምሌ 10 ቀን 2004 ዓ.ም

ዳኞች፦ ፀጋዬ ወርቅአየሁ
ጌትነት መንግሥቴ
ተፈሪ ገብሩ
አንዳርጌ ላቀ
ኃ/ማርያም ሞገሥ

አመልካች …አዳሙ ያዛቸው
ጥገቴ ያዛቸው
መልካሙ ያዛቸው
ሰንደቁ ያዛቸው
ይርጋ ያዛቸው ------ወኪል አዳሙ ያዛቸው ቀረቡ
አበበ ያዛቸው
አገሬ አዛኘ
ናፈቀ ያዛቸው
በጎሳ ያዛቸው

*ተ ጠ ሪ ………. ነገሱ ዘገየ --------ወኪል ሲስተር ማናለብሽ ያዛቸው ቀረቡ*

*መዝገቡ ያደረው ለምርመራ በመሆኑ መርምረን የሚከተለውን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡*

**ፍርድ**

*ከመዝገብ ምርመራው እንደተረዳነው በግራ ቀኙ መካከል የተነሳው የውርስ ክርክር በሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ አግኝቷል፡፡ አፈፃፀሙ በዚሁ ፍርድ ቤት ሲመራ ቆይቶ ታህሣሥ 201 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ፍርድ ቤቱ ተጠሪ በጂ ይገኛል የተባሉትን ንብረቶች በየድርሻቸው እንዲያከፋፍል የአምባ ጊዮርጊስ ከተማ አስተዳደርን አዟል፡፡ የክፍሉ ቀበሌም በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ማከፋፈሉን፤ ነገር ግን ቤትን ለማከፋፈል ባለሙያ የሚያስፈልግ መሆኑን፤ ተጠሪ ላሟን ለማካፈል ፈቃደኛ አለመሆኗን ገልጿል፡፡ በድጋሚ ትዕዛዝ ተላልፎለታል፡፡ ቀበሌው እንደፍርዱ አስፈጽሟል ማለት ስለማይቻል ቤቱን በጨረታ ለመሸጥ ተገምቶ ይቅረብ ተባለ፡፡ ላም ከነጥጃዋ እና ፍየል ተገምቶ እንዲቀርብም ታዘዘ፡፡ ከዚህ በኋላም ንብረቶቹ በጨረታ እንዲሸጡ ሐምሌ 22 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተወስኗል፡፡ ግራ ቀኙ አልተካፈሉም የተባለውን ቤት በተመለከተ ምስክሮችን ሰምቶ እንዲያስፈጽም የወረዳው ፍርድ ቤት ታዘዘ፡፡*

*በዚሁ መሠረት የወረዳው ፍርድ ቤት ፍርዱን ስለማስፈጸሙ በመግለጽ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን በሌሎች ንብረቶች ላይ*

*ፍርዱን በማስፈጸም ላይ ለነበረው ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ያቀርባል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ከተመለከተ በኋላ በሰጠው ውሳኔ የወረዳው ፍርድ ቤት በውክልናው መሠረት የሠጠው ውሳኔ ወካዩ የከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሰጠው የሚቆጠር በመሆኑ ይግባኙ መቅረብ ያለበት ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው ሲል ወስኗል፡፡*

*ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ሲሆን ፍርዱ ሳይፈጸም እንደተፈጸመ ተቆጥሮ መዝገቡ መዘጋቱ ተገቢ አልነበረም፤ የከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህን ማረም ሲገባው ማለፉ ተገቢ ባለመሆኑ ፍርዱ ይሻርልኝ የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሏ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ግድፈት የለበትም በማለት ፍርዱ እንዲጸናላት ጠይቃለች፡፡ ክርክሩም በዚሁ ተጠናቋል፡፡*

*እኛ መዝገቡን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም ግራ ቀኙን ከሚያከራክራቸው ሃብት ውስጥ ቤትን በተመለከተ የሰሜን ጎንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አፈፃፀሙንም ሲመራ ቆይቶ በመጨረሻ የተፈጠሩትን ተግባራዊ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የወገራ ወረዳ ፍርድ ቤት በቤት ላይ የተሰጠውን ፍርድ እንዲያስፈጽምለት ወክሎ በሌሎች ንብረቶች ላይ የሰጠውን ፍርድ በራሱ ማስፈፀሙን ቀጥሏል፡፡ በዚሁ መሠረት የወገራ ወረዳ ፍርድ ቤት በቤቱ ላይ የተሰጠውን ፍርድ ማስፈጸሙን በመግለጽ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካች ግን እንደፍርዱ ሳይፈፀም ተፈፅሟል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት ቅሬታ ተሰምቷቸዋል፡፡ ይህን ቅሬታቸውን በሌሎች ንብረቶች ላይ አፈፃፀሙን ለቀጠለው (የሰሜን ጎንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለወረዳው ፍርድ ቤት ውክልና በሰጠበት መዝገብ ላይ ነው) ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በሰጠሁት ውክልና መሠረት የወረዳው ፍርድ ቤት ፍርዱን በማስፈጸም ሂደት የሰጠው ትዕዛዝ እኔ እንደሰጠሁት የሚቆጠር በመሆኑ በትዕዛዙ ላይ የተነሳውን ቅሬታ እኔ ለማየት አልችልም በማለት ቅሬታውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡*

*የቅሬታውን አቀራረብ እንዳየነው በቀድሞው መዝገብ ላይ የሚቀጥልበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ ራሱን በቻለ መንገድ አዲስ ይግባኝ መዝገብ ተከፍቶ ሊታይ ይገባ ነበር፡፡ ቅሬታው አሁን የቀረበበት መንገድ የክርክሩን ይዘት መልክ እንዲያጣ፣ ክርክሩን በአግባቡ ለመገንዘብ የሚያዳግት፤ ነገሩን ለማጥራት እና በተገቢው መንገድ ለመምራትም አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያደርግ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ክርክሮችን በአግባቡ ተረድቶ በተቀላጠፈ መንገድ ለመወሰን ያለውን ዕድል ያጠባል፡፡ የሥነ-ሥርዓት ህጉ በተቀላጠፈ መንገድ ውጤታማ ውሳኔ ለመስጠት ያለውን ግብ ያሰናክላል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውክልና በሰጠበት መዝገብ ላይ አመልካች ይግባኝ ሲያቀርብለት ራሱን በቻለ መንገድ አዲስ የይግባኝ መዝገብ እንዲያስከፍት ማድረግ ሲገባው አቀራረቡ ትክክል እንደሆነ አድርጎ በመውሰድ በፍሬ ጉዳዩ ላይ የቀረበውን ቅሬታ ለማየት ሥልጣን የለኝም ሲል መወሰኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በቅድሚያ አቀራረቡ መታረም ይገባው ነበር፡፡*

*ጉዳዩ አሁን ባለበት ደረጃ ግን የከፍተኛው ፍርድ ቤቱ ከወሰደው አቋም አንፃር ጉዳዩ ወደኋላ ተመልሶ አመልካች አቤቱታውን በሌላ መዝገብ እንዲያቀርብ እና ፍርድ ቤቱም የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን መመለስ የባለጉዳዩን ጊዜ እና ገንዘብ የሚበላ*

*በመሆኑ ተገቢ ሆኖ ባለማግኘታችን የተፈጠረውን ግድፈት በማለፍ አመልካች በፍሬ ነገሩ ላይ ያቀረበውን ቅሬታ መመርመሩን መርጠናል፡፡*

*የከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ቅሬታ ላለመቀበል የሰጠው ምክንያት የወረዳው ፍርድ ቤት በውክልና መሠረት የሰጠው ማናቸውም ትዕዛዛት እኔ እንደሰጠሁት የሚቆጠር በመሆኑ በማስፈጸሙ ሂደት የሚነሱት ቅሬታዎች ለጠቅላይ ፍርድ ቤት እንጂ ለከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ሊቀርቡ የሚችሉ አይደለም የሚል ነው፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ እንዲያስፈጽምለት ለወረዳው ፍርድ ቤት ውክልና ሲሰጥ የወረዳው ፍርድ ቤት በአፈፃፀሙ ሂደት የሚሰጣቸው ትዕዛዛት የከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሰጠው የሚቆጠር መሆኑ ዕውነት ነው (የፍ.ብ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ 374)፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ይግባኝ ባልተባለባቸው የአፈፃፀም ትዕዛዛት ላይ ብቻ ነው፡፡ በትዕዛዙ ላይ ይግባኝ የሚባልበት ሁኔታ ሲኖር ግን ትዕዛዙን የከፍተኛው ፍርድ ቤት እንደሰጠው ሳይሆን የወረዳው ፍርድ ቤት ራሱ እንደሰጠው ይቆጠራል፡፡ ይግባኝ የሚቀርብበት ትዕዛዝ ሲኖር የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን ሊመለከት ይችላል ማለት ነው፡፡ የፍትሐ-ብ ሥነ-ሥርዓት ህጉ የእንግሊዝኛው ቅጂ በዚህ መንፈስ የተቃኘው በዚህ መንገድ ነው፡፡ የአማርኛው ቅጂ ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የወሰደውን አቋም የሚደግፍ ነው፡፡ በአማርኛው እና በእንግሊዝኛው ቅጂ ላይ እንዲህ ያለ መጣረስ ሲኖር የህጉን መሠረታዊ ግብ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነገሩን ማየት የሚገባ ይሆናል፡፡ በመርህ ደረጃ ፍርድን የሚያስፈጽመው ፍርዱን የፈረደው ፍርድ ቤት ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ፍርድን እንዲያስፈጽም ሌላ ፍርድ ቤት አይወከልም ማለት አይደለም፡፡ ለአፈፃፀም አመቺነት ሲባል ፍርዱን እንዲያስፈጽም ሌላ ፍርድ ቤት ውክልና ሊሰጠው ይችላል፡፡ ውክልና የተሰጠው ፍርድ ቤት ውክልናውን ከሰጠው ፍርድ ቤት ሥልጣን ጋር ዕኩል ሆኖ የሚቆጠር ቢሆንም እንደእንግሊዝኛው ቅጂ አባባል ይግባኝ የሚቀርብባቸው ትዕዛዛት ሲኖሩ ራሱ ተወካዩ እንደሰጠው ይቆጠራል፡፡ ይህ መባሉ የራሱ የሆነ አገልግሎት አለው፡፡ በእኛ ዕምነት ውክልና ሰጪው የበላይ ፍርድ ቤት ከተወካዩ ፍርድ ቤት ጋር በሁሉም ጉዳይ ላይ (ይግባኝ በሚባልባቸው ነጥቦች ጭምር) ዕኩል ሥልጣን እንዳለው መቁጠር በበታች ፍርድ ቤቶች እና በበላይ ፍርድ ቤቶች መካከል ያለውን የልምድ እና የትምህርት ዝግጅት ከዚሁ ጋር ተያይዞም በፍርድ ጥራት ረገድ ያለውን ልዩነት የሚያጠፋ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በሥነ-ሥርዓት ህጉ የሥልጣን ዕርከን ልዩነት በመፍጠር ረገድ ህጉ ሊያሣካ የተፈለገውን ግብ የሚያሰናክል፣ ዝቅ ለሚሉ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ውክልናዎችን ተገቢነትም (legitimacy) ጥያቄ ውስጥ የሚጥል ይሆናል፡፡ ይልቁንም በአንድ በኩል ጉዳዮችን በተቀላጠፈ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማየት፣ በሌላ በኩል በልምድ እና በትምህርት ዝግጅት ዕጥረት ምክንያት የሚፈጠረውን የተወካዩን ፍርድ ቤት ሥህተት እዚያው በቅርብ ለሚገኘው ወካዩ ፍርድ ቤት እንዲታይ ማድረግ የይግባኝ መብት በማጣበብ ረገድ የሚመጣውን ችግር በማስወገድ ፍትሐዊነትን ማስፈን ይቻላል፡፡ የሥነ-ሥርዓት ህጉ የእንግሊዝኛው ቅጂ እነኚህን መሠረታዊ የሆኑ የፍትሐ-ብሄር ህግ ዓላማዎች የሚያሳካ ነው፡፡ ስለሆነም የሥነ-ሥርዓት ህጉ ሊያራምድ ከሚፈልገው ግብ አንፃር ተጣጥሞ የሚሄደው የእንግሊዝኛው ቅጂ ነው የሚል ዕምነት አለን፡፡ በዚህ የተነሳም ልንከተለው የሚገባን ይህን ሊሆን ይገባል፡፡*

ስለሆነም እንደእንግሊዝኛው ቅጂ አገላለጽ የወገራ ወረዳ ፍርድ ቤት በተሰጠው ውክልና መሠረት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የሚቀርብበት ትዕዛዝ ሲኖር ይግባኙን ማየት ያለበት ውክልናውን የሰጠው የሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆን አለበት፡፡ ከዚህ አኳያ የተጠቀሰው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም ሲል ሰጠው ትዕዛዝ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የቀረበለትን ቅሬታ ተመልክቶ በፍሬ ጉዳዩ ላይ የመሰለውን ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ይሆናል፡፡ ይህ ሲሆን ግን ከፍ ሲል እንደጠቀሰው ክርክሩ ሊቀጥል የሚገባው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሌሎችን ንብረቶች ለማስፈጸም በቀጠለው የአፈፃፀም መዝገብ ላይ ሳይሆን ራሱን የቻለ የይግባኝ መዝገብ ተከፍቶ ሊሆን ይገባል፡፡ የቀረበውን የንብረት ማስከበር ጥያቄ በተመለከተ ፍሬ ጉዳዩ ዕልባት የተሰጠበት እና ጉዳዩን በያዘው ፍርድ ቤት ሊስተናገድ የሚችል በመሆኑ አልፈነዋል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

የወገራ ወረዳ ፍርድ ቤት ከሰሜን ጎንደር መስተዳደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጠው ውክልና መሠረት በሰጠው ትዕዛዝ አመልካች ቅር ተሰኝቶ ያቀረበው ይግባኝ ራሱን የቻለ የይግባኝ ፋይል ተከፍቶለት እንዲቀርብ ማድረግ ሲገባው የፍርዱን ሌላ ክፍል ለማስፈጸም በያዘው መዝገብ ላይ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀብሎ ማስተናገዱ ተገቢ ካለመሆኑም በላይ ቅሬታውን ለማስተናገድ ሥልጣን የለኝም ሲል መወሰኑ ከሥነ-ሥርዓት ህጉ ዓላማ ጋር የሚጣጣም ሆኖ ባለማግኘታችን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ ሽረናል፡፡ ኪሣራና ወጪ ይቻቻሉ፡፡

## ትዕዛዝ

የሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርደ ቤት ፍርዱ የተሻረ መሆኑን አውቆ አመልካች ያቀረበውን ቅሬታ ራሱን የቻለ ሌላ የአፈፃፀም ይግባኝ ፋይል እንዲከፈት በማድረግ ፍሬ ጉዳዩን ተመልክቶ የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡

በዚህ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም ግልባጩ ይተላለፍለት፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የአብላጫው ድምጽ ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

**የሃሣብ ልዩነት**

እኛ ስማችን በ3ኛና 4ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰው ዳኞች ከሌሎች የስራ ባልደረባቻችን በአብላጫ ድምጽ በሰጡት ውሳኔ ላይ በሀሳብ እንደሚከተለው ተለይተናል፡፡ በመሠረቱ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ሰባተኛ መጽሐፍ ስለ ፍርድ አፈፃፀም በሚለው መጽሐፍ ላይ አፈፃፀምን አስመልክቶ የተደነገገ መሆኑ ያታወቃል፡፡ መርሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 371 ላይ የተቀመጠ ሲሆን ፍርድን የሚያስፈጽመው ፍርድ ቤት ፍርዱን የሰጠው ወይም እንደ ፍርዱ እንዲያስፈጽም የታዘዘ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አሁን ክርክሩ የተነሳው እንደ ፍርዱ እንዲያስፈጽም የታዘዘው ፍርድ ቤት

*ፍርዱን ከሰጠው ፍርድ ቤት ያነሰ የሥልጣን ደረጃ ሲኖረው የይግባኝ ሥርዓቱ ምን መሆን አለበት የሚለው ነው፡፡*

*በእርግጥ በፍታብሔር ሕጉ ላይ የስር ፍርድ ቤት የሆነው ለአፈፃፀሙ አመቺነት ሲባል መወከል የሚቻል መሆኑ አልተከለከለም፡፡ ወካዩ ፍርድ ቤትም ተወካዩን ፍርድ ቤት ችግሮች ሲያጋጥሙት የሚቆጣጠር ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 374/2/ ላይ ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ ተወካዩ ፍርድ ቤት በስልጣን ያነሰ ቢሆንም ወካዩ ፍርድ ቤት በቅርበት የሚከታተለው መሆኑን ያሳያል፡፡ በዚሁ ምክንያትም በውክልና ራሱ የሰጠውን ጉዳይ በይግባኝ ራስህ ተመልከት ሌላውን በውክልናህ ተቆጣጠር የሚለው የስልጣን መቀላቀልን የሚፈጥርና የፍትሐዊነት መርህን የተከተለ አይሆንም፡፡*

*ስለ ይግባኝ ስርዓቱም የፍታብሄር ሕግ በቁጥር 374/1/ ላይ በግልጽ ፍርዱን እንዲያስፈጽም የተወከለው ፍርድ ቤት ፍርዱን ከሰጠው ፍርድ ቤት ጋር ዕኩል ስልጣን እንዳለው ይቆጠራል በማለት ግምት ወስዷል፡፡ ግምት መውሰድም ይህን መቀላቀል ለማስወገድ ታስቦ የተደረገ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ የአብላጫው ድምጽም የአማርኛው የፍትሐብሔር ሕጉ አባባል ይህ መሆኑን ተቀብለው የእንግሊዝኛው ትርጉም ሚለውን በመቀበል ነው፡፡ በእኛ በኩል የእንግሊዘኛው አገላለፅ የአብላጫው ድምፅ የሚለውን ቢመስልም የአማርኛው ትርጉም ግን የተለየ ስለሆነ በሀገራችን ከሕገ መንግስቱ የትርጉም መርህ ጅምሮ አማርኛ ልዩነት ባለ ጊዜ የበላይነት ስላለው በአማርኛው ትርጉም በመሄድ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በይግባኝ አልመለከትም ማለቱን መሻር አይገባውም ነበር፡፡ መሰረታዊ የሕግ ስህተተም የለበትም፡፡*

*ስለዚህ የአብላጫው ድምጽ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በውክልና እንድፈፀም የላከውን የፍርድ አፈፃፀም በይግባኝ መመልከት አይገባኝም ማለቱ የሚነቀፍ አልነበረም በማለት በሀሳብ ተለይተናል፡፡*